**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት**
**The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order**
www.ethiopianorthodox.org

# ዓመታዊ ሪፖርት

## እንኳን ለዘመነ ማርቆስ በሰላም በጤና አደረሳችሁ!!

ይህ ዌብ ሳይት ከተጀመረ (ጃንዋሪ 1 ቀን 2003) ሰባተኛ ዓመቱን ይዟል። በተቻለን አቅም የቤተ ክርስቲያና ችንን እምነቷ፣ ሥርዓቷ እንዲሁም ታሪኳን በሙሉ እዚህ ዌብ ሳይት ማስፈር ባይቻልም ዋና ዋናውን ክፍል ተከታይ ምዕመናኖቿ ማወቅ ያለባቸውን ለማሳወቅ የተቻለንን እየጣርን ነው። ዌብ ሳይቱ አገልግሎት መስጠት ከጀምረ አስንስቶ በተቻለ አቅም አብዛኛውን ጊዜ በሳምንት አንድ ጊዜ ተጨማሪ ትምህርታዊ ጽሑፎችን በማውጣት ምዕመናን ስለ እምነታቸው የበለጠ እንዲያውቁ  እየሞከርን ነው።

ይህን አገልግሎት መስጠት ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ የመጣውም የጎብኝዎች ቁጥር በአሁኑ ወቅት በወር ወደ 5 ሚሊዮን ደርሷል። ለጊዜው በዚህ ዌብ ሳይት ላይ ወደ 10,000 ሺህ ገጽ የሚጠጋ ጽሑፍና ከ250 ሰዓት በላይ ስብከትና ዜማዎች ቀርቧል። ከቤተ ክርስቲያናች ቅርስና ትምህርቷ አኳያ ይህ ዌብ ሳይት ገና በጣም በጣም ጥቂት የሆነ ትምህርታዊ ጽሑፎችን የያዘ ሲሆን ነገር ግን ብዙ ተጨማሪ ትምህርቶችና መጻሕፍት ወደፊት ለመጨመር ዕቅድ አለ። አሁንም ብዙ የተወጠነ ዕቅድ ስላለ በዚህ ቅዱስ ተግባር ለመተባበር የምትፈልጉ ካላችሁ ከአምላካችን ዘንድ በረከት የምትቀበሉበት ስለሆነ በምን ዓይነት መርዳት እንደምትችሉ እንድትጽፉልን አደራ እንላለን። በአለፉት ዓመታት ሪፖርት ላይ የጀርመንኛና የፈረንሳይኛ ቋንቋ ድኅረ ገጾች የተዘጋጁት ከሌላ ዌብ ሳይቶች ጋር በማገናኘት መሆናቸውንና ነገር ግን ዓላማችን ሁሉም በውጭ ቋንቋ የተዘጋጁት ጽሑፎች አንድ ዓይነት መልእክት እንዲኖራቸው ነው ማለታችን ይታወሳል። በዚህም መሠረት በጀርመን ሀገር በሃኖቨር ከተማ የሚኖሩት አቶ ክንፈ ገብረ ኢየሱስ በእንግሊዘኛ ድኅረ ገጽ ላይ የወጡትን፤ ከምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ በስተቀር በሙሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተርጉመው የጀርመንኛው ገጽ የተሟላ እንዲሆን ማድረጋቸው ይታወሳል። አሁን ደግሞ በደቡብ ፈረንሳይ Arles ከተማ የሚገኘው Roots and Culture የተባለው ድርጅት የሀገራችን ባሕልና እምነት በደንብ እንዲተዋወቅ ልክ እንደ ጀርመንኛው የእንግሊዘኛውን ጽሑፎች ወደ ፈረንሳይኛ መተርጎም ጀምረዋል። እግዚአብሔር አምላክ ሥራቸው የተቃና እንዲሆንላቸው ፤ከፍጻሜ ሲደርስም ብዙዎች የሚጠቀሙበት እንዲሆን እንጸልያለን።

በ2007 የተጀመረው የቆሎ ትምህርት ቤት ከተጠበቀው በላይ ጎብኚዎች ያሉት ሲሆን የጎደሉትን ትምህርቶ ች በብዛት ተሟልቶ አገልግሎቱ ቀጥሏል። በቅርቡም የመልክዐ ማርያምን ፤ መልክዐ ኢየሱስንና የመዝሙረ ዳዊትን አነባበቡን በግእዝ እናቀርባለን። በዚህ ቆሎ ት/ቤት ላይ የተዘረዘሩትን ትምህርቶች አጥንተው ከጨረሱ አቅራቢያዎ ወዳሉት ሊቀ ጳጳስ በመሄድ የሚሰጠውን ፈተና ወስደው ካለፉና ሊቀ ጳጳሱ ሌሎችንም መመዘኛዎች ጠይቀዎት ካለፉ የድቁና ሥልጣነ ክህነት መቀበል ይችላሉ።

ከዚህ በታች የተጠቀሱት ደግሞ ታቅደው ያልተፈጸሙ ነገር ግን ለሚቀጥለው ዓመት ለመሥራት የታቀዱ ናቸው፤

1) ለመናፍቃን መልስ ተብለው የቀረቡትን ወደ ውጭ ቋንቋዎች ማስተርጎምና ማቅረብ፤

2) ተጨማሪ መጻሕፍትን ማቅረብ፤

ከሞላ ጎደል የሠራነውና ልንሠራው ያቀድነው ይህ ሲሆን በዚህ ላይ ልትተባበሩና ወይም አስተያየት ያላች ሁ ጻፉልን። ዜማዎች ወይም ጠቃሚ ጽሑፎች ካላችሁ ብትልኩልን ደግሞ ሌሎች ወገኖቻችን ሰምተው የ ሚጠቀሙበት ይሆናል።

**በዚህ አጋጣሚ እዚህ ዌብ ሳይት ላይ የሚወጡ ጽሑፎችን ታይፕ በማድረግ እየተባበሩን ላሉት በካሊፎርንያ ለሚኖሩት ለአቶ ስንታዩሁና አቶ ደረጀ አጐናፍር እንዲሁም በኢትዮጵያ ለምትገኝዋ ለወ/ሮ ራሔል አበበ ከልብ የመነጨ ምስጋና እያቀረብን ይህ አስተዋጿቸው እንደሚቀጥል ተስፋ እናደርጋለን። እግዚአብሔር አምላክ በበረከቱ እንዲጎበኛቸውና የልባቸውን ሐሳብ እንዲፈጽማላቸው እንጸልያለን።**

**እግዚአብሔር አምላክ አዲሱን ዓመት የሰላም ፤ የደስታ ፤ እንዲያደርግልን ፤ ለሀገራችን ኢትዮጵያ ሰላምንና በረከትን፣ ለሕዝባችንም አንድነትንና ፍቅርን ይስጥልን።**

www.ethiopianorthodox.org team!

September 2010

**ዌብ ማስተር**

**በእደ ማርያም እጅጉ ረታ**